የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

## የኢትዮጵያ የፓለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የሰሜን አሚሪካ ቅርንጫፍ

9/15/2014

# ሶሴፕ አሜሪካ ወኪሉን ወደ ዊኒ ፔግ ይልካል



የካናዳውያን ሰብዓዊ መብት ቤተመዘክር ይህ ነው

በካናዳ ዊኒፔግ የስብዓዊ መብት ሙዚየም ከ2008 ጀምሮ ሲታነጽ ቆይቶ የፊታችን ሴፕቴምበር 20 በከፍተኛ ድምቀት ለሕዝብ ዕይታ ክፍት ይሆናል፡፡ የካናዳ ሰብዓዊ መብት ቤተመዘክር ዋናው ኣላማው 1ኛ ስለ ሰብዓዊ መብት ዕውቀትና ግንዛቤ ለማስጨበጥ 2ኛ ለሌላውም ወገን ከበሬታ ለማጎናጸፍና 3ኛ ውይይት፣ ግንዛቤንና ተርባራዊነትን ለማበረታታ ነው፡፡ በዚህ ቤተመዘክር ውስጥ በዓለም ዙሪያ ስለሰበዓዊ መብት የተደረጉትን ታሪካዊ እንቅስቃሴዎችን ከሴፕቴምበር 20, 2014 ጀምሮ በቃዋሚነት ለሕዝብ ክፍት ያደርጋል፡፡

በሴሶፐ አለም አቀፍ ፐሬዚዳንት **አቶ አሊ ሁሴን** ታሪክ ላይ በመንተራስ በኢትዮጵያ የግማሽ ሚሊዮን ሕዝባችንን የጨፈጨፈው የደርግ **ቀይ ሽበርን** የሚያጋልጠው ሃቅ ለጎብኚዎች ሲቀርብ የሚያስከትለውም ውጤት ትምህርት ሰጭ እንደሚሆን ታላቅ እምነት አለ፡፡

ሶሴፐ ካናዳ በዊኒፔግ ድንቅ ስራዎችን ለረጅም ዓመታት ለሕዝብ ሲያስተዋውቅና ሲያስተምር መኖሩን በየአመቱ ከሚያካሄደው **“መዳረሻቸው ስለጠፋው እስረኞች**” ዝግጅትና **“ለሙብትህ ሩጥ**” የሚለው ዝግጅት ሶሴፐ በዊኒፔግ ካናዳ ከፍተኛ የሕዝብ አድናቆትን ኣትርፎለታል፡፡ በጠንካራ የስራ ውጤቱም ከታዋቂ የሰብአዊ ሙብት ድርጅቶች ተርታ እንዲሰለፍ አብቅቶታል፡፡ አሊ “ዝምታን መስበር” በሚል መፈክር ስለ ቀይ ሽብርና መዳረሻጨው ስለጥፋው የፓለቲካ እስረኞች ሃቁን ገሃድ የሚያደርግበት ልይ ስፍራ በዚህ ቤተመዘክር ውስጥ አግኝቷል፡፡ ይህን ሙዚዬም በቅድሚያ ለመገንባት የ21 አገር ከ40 በላይ ተወዳዳሪዎ  አርክቴክተሮች ማመልከቻ አቅርበው አሸናዊው የሆነው የ Albuquerque, New Mexico አርክቴክቸር አንቶኔ ፐሬዶክ ነው፡፡ አስካሁን ድረስ ግንባታውን ለማከናወን ከ$400 ሚሊዮን በላይ ፈጅቷል፡፡ ሕንጻው እንዲቆም የተመረጠበት ቦት በራሱ ታሪካዊ ነው፡፡ ይህ ቤተመዘክር  **የሆሎኮስትን፣ በካናዳውያን አቦርጅናሎች ላይ ስለተፈጸመው ግፍና ሌሎችንም በአለም ዙሪያ በርካታ የሰበዕዊ ሙብት መረገጥን** ለጎብኚዎች ያቀርባል፡፡ ኢትዮጵያን አስመልክቶ የደርግ ፋሽስታዊ መንግስት በቀይ ሽብር ስም ከግማሽ ሚሊዎን  ሕዝባችንን በጠራራ ፀሃይ እንደ ክብት አርዷል፡፡ ያንድ ሰው ሕይወት መቀጨት የለበትም ስንል የተቀጨው ግን ከ500 ሺ ሕዝብ በላይ እንደሆን ሲታወቅ ኢትዮጵያችን የደም ጎርፍ እንዳጠቀለቃት ተዘግቧል፡፡ ይህ ታሪክ ነው በዊኒፔግ ባሙት እስከ ሁለት ሚሊዮን ጎብኚ የሚመለከተው፡፡ ስለ ሰብ አዎ ሙብት መከበር በሕይወት ካለው ይልቅ በግፍ የተገደለው ሙታን ሳይተነፍሱ የሚያስተላልፉት መልዕክት ሃያል ነው፡፡  መልዕክታቸውም የሚለው ይህን መሰል ግፍ ዳግም መፈጸም የለበትም ነው፡፡ አለማችን በበቂ የሆሎኮስትን እልቂት አይታለች፡፡ ኢትዮጵያችን የቀይ ሽብርን ሰቆቃ አይታለች፡፡ በቀለም ልዩነት፣ በዘርና በሃይማኖት ልዩነት አለማችን ይህ ነው ተብሎ የማይገለጽ ግፍ አይታለች፡፡ በኢትዮጵያችን የደርግን ጣረሞት የተላበሰው ወያኔ ቀይ ሽብርን ቅውጥሎበታል፡፡ Surviving The Red Terror (A Fighting Woman's Tale) በሚለው መጽሃፍዋ መቅደም ላይ ባቢሌ ቶላ እንዲህ ይላል

“. . . **The Derg is dead and buried and yet resurreacted by the TPLF. The rule by gun, the violence of the State continues . . . The Terror has no name, no designate colour, but it is there, the victims fall one after the other. . . “**




አሊ ሁሴን ለሰብዓዊ ሙብት መከበር በተለይም የደርግ ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ላወረደው የሕይወትና የስነልቦና ጥፋት ደከመኝ ሳይል ፐሬዘዳንት ሆኖ በሚያገለግለው ሶሴፐ መልዕክቱን እያስተላለፈና እያስተማረ ይገኛል፡፡ የቀይ ሽብር ታሪክ በራሱ በአሊ ታሪክ ተሞርክዞ በካናዳው የሰበዓዊ ሙብቶች ሙዚየም ለመታየት በሙብቃቱ ጀግናውን አሊንና ድርጅቱን ሶሴፐን እንኮራባቸዋለን፡፡ የአሊ የቀይ ሽብር ታሪክ ከላይ በተጠቀሰው ታሪክዋ ቆንጅት እንደገለጸችው “ **My story is just one of the many, part of the many, an experience on its owns** “ አሊም ከሚሊዮኖቹ  የቀይ ሽብር  ሰለባ አንዱ ነው፣ ታሪኩም የሚሊዮኖች አካል ነው፣ የድርሻው ተመክሮ ነው፡፡ አሊ አበክሮ እንደሚለው “ ስለ ደርግ ቀይ ሽብር የምናነሳው ብቀላን ለማካሄድ ሳይሆን ይህ መሰል ግፍና ኢሰብዓዊ ግፍ ዳግም እንዳይፈጸም ትምህርት ለመስጠት ነው፡፡”

በዚህ ቤተ መዘክር ውስጥ በሙቶ የሚቆጠሩ ታላላቅ የስብዓዊ ሙብት ተከራካሪ ስዎች ታሪክ ሲቀርብ ከፍተኛ ግምት ከተሰጣቸው አስሮቹ ውስጥ የአሊ ታሪክ አንዱ ነው፡፡ ከነማንዴላ ተርታ መሰለፍ ዕድል ሳይሆን የስራ ውጤት ነው፡፡

ሴፕቴምበር 20 ተመርቆ ለሕዝብ ክፍት የሚሆነውን የዚህን ታላቅ የካናዳውያንን የሰብዓዊ ሙብት ሙዚየም በተለይም የቀይ ሽበርን ታሪክ በሙዚየሙ እንዲታይ ላበቃው አለም አቀፍ የሶሴፐ ድርጅትና ለፐሬዘዳንቱ ለአቶ አሊ ሁሴን ድጋፍ ለመስጠትና አድናቆታችንን ለማቅረብ የሰሜን አሜሪካ የሶሴፐ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ልዑካኑን ይልካል፡፡ የካናዳ ሙዚየም ዓይነቱ በየአሕጉራቱ ይፈጸም ዘንድ ትግላችን ይቀጥላል፡፡